በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ኅዳር ፲፰ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

- ‹‹በዚህም ወር በሀያ አራተኛው ቀን የእስራኤል ልጆች ጾመው፥ ማቅም ለብሰው፥ በላያቸውም ትቢያ ነስንሰው ተከማቹ። የእስራኤልም ዘር ከእንግዶች ሁሉ ራሳቸውን ለዩ፥ ቆመውም ኃጢአታቸውንና የአባቶቻቸውን ኃጢአት ተናዘዙ። በየስፍራቸውም ቆመው የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን የሕግ መጽሐፍ የቀን ሩብ ያህል አነበቡ ሦስት የቀን ሩብም ያህል ተናዘዙ፥ ለአምላካቸው ለእግዚአብሔርም ሰገዱ።›› ***ነህ 9፡1-3፡፡*** በሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ከፈጸሙ በኋላ ማቅ ለብሰው፣ ትቢያ ነስንሰው ጾሙ፡፡ ይህም የትህትና ምልክት ነበር፡፡
- ከእንግዶች (ከውጪ) ሰዎች ራሳቸውን ለይተው ኃጢአታቸውንና የአባቶቻቸውን ኃጢአት ተናዘዙ፡፡
- በጥንት ዘመን ሰዎች በሰዎች ሁሉ ፊት ኃጢአታቸውን ይናዘዙ የነበረ ቢሆንም አሁን በዘመነ ሐዲስ ግን ኑዛዜ/ንስሐ በምድር የእግዚአብሔር ወኪል በሆነ ካህን ፊት በግል የምንፈጽመው ነው፡፡
- አንዳንድ ሰዎች ኑዛዜን እንደ ቀላል ሲቆጥሩት ሌሎች ደግሞ ጨርሰው ከመናዘዝ ርቀው ይታያሉ፡፡
- እኛ ግን ዘወትር ኃጢአታችንን የመናዘዝን ሕይወት አጥብቀን መያዝና ይልቁንም መንፈሳውያን በዓላትን በፍጹም መንፈሳዊ ደስታ በእግዚአብሔር ደስ እያለን ማክበር ይቻለን ዘንድ ንስሐ ገብተን ቅዱስ ቁርባን በመቀበል እናክብራቸው፡፡
- እስራኤላውያን በዚያን ጊዜ ቀኑን ለመንፈሳዊ ነገር በመከፋፈል የቀኑን አንድ አራተኛ የእግዚአብሔርን ቃል አነበቡበት - ተሰበኩበት የተረፈውን የቀኑን ሦስት አራተኛ ደግሞ ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር በመስገድ፣ ምስጋና በማቅረብ፣ ኃጢአታቸውን ለመናዘዝ ተጠቀሙበት፡፡ እኛ ግን ለማንበብም ሆነ ለመጸለይ ስንፍና አይታይብንምን?
- በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በተለይ በዕለተ ስቅለት (በሰሙነ ሕማማትና) በሌሎችም የአገልግሎትና የአምልኮት ሥርዓት የምናደርገው ሁሉ እንደተጠቀሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተማርነው ነው፡፡

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱</u>

- ‹‹ሌዋውያኑም ኢያሱና ባኒ፥ ቀድምኤል፥ ሰበንያ፥ ቡኒ፥ ሰራብያ፥ ባኒ፥ ክናኒ በደረጃዎች ላይ ቆመው ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር በታላቅ ድምፅ ጮኹ። ሌዋውያኑም ኢያሱ፥ ቀድምኤል፥ ባኒ፥ አሰበንያ፥ ሰራብያ፥ ሆዲያ፥ ሰበንያ፥ ፈታያ እንዲህ አሉ። ቆማችሁ ከዘላለም እስከ ዘላለም አምላካችንን እግዚአብሔርን ባርኩ። እንዲህም በሉ። በበረከትና በምስጋና ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያለው ክቡር ስምህ ይባረክ።›› ***<u>ነህ 9፡4-5፡፡</u>***
- **ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን በቅዳሴውና በሌሎችም አገልግሎቶች እንደምናደርገው ሌዋውያኑም ዝማሬውን አዘጋጅተው ሲያመሰግኑ ሕዝቡም እየተቀበሉ አመሰገኑ፡፡ ምስጋናቸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናገኛቸው ምስጋናዎች እጅግ ያማረና የተዋበ ነው፡፡ በምዕራፉ የምናገኘውም** ‹‹ቆማችሁ ከዘላለም እስከ ዘላለም አምላካችንን እግዚአብሔርን ባርኩ።›› **የሚለው ምስጋና ለእስራኤል ከተደረገላቸው ድንቅ ሥራ የተነሳ የቀረበ ምስጋና ነው፡፡ ቅዳሴውን፣ ማኅሌቱን፣ ሰዓታቱን፣ ኪዳኑንና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶችን በመቆም የምንፈጽመውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡**
- ‹‹አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ ሰማዩንና የሰማያት ሰማይን ሠራዊታቸውንም ሁሉ፥ ምድሩንና በእርስዋ ላይ ያሉትን ሁሉ፥ ባሕሮቹንና በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ፥ ፈጥረሃል፥ ሁሉንም ሕያው አድርገኸዋል የሰማዩም ሠራዊት ለአንተ ይሰግዳሉ።›› ***<u>ነህ 9፡6፡፡</u>***
- **‹‹እግዚአብሔር ሆይ ሰማይን፣ ምድርን፣ ባሕርን … በኋላም ሰውን የፈጠርህ ከበደለም በኋላ ወደ ክብሩ የመለስከው አንተ ነህ›› በማለት የሥነ ፍጥረትን ነገር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተናገሩ፡፡ ‹‹ሰውን ፈጥረህ ለዘላለም የምትጠብቀው የሚያገለግሉህ ረቂቃን መላእክትንም የፈጠርህ አንተ ነህ፡፡›› አሉት፡፡**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

- ‹‹አንተ እግዚአብሔር አምላክ ነህ አብራምን መረጥህ፥ ከዑር ከላውዴዎንም አወጣኸው፥ ስሙንም አብርሃም አልኸው ልቡም በፊትህ የታመነ ሆኖ አገኘኸው የከነዓናዊውንና የኬጢያዊውን የአሞራዊውንም የፌርዛዊውንም የኢያቡሳዊውንም የጌርጌሳዊውንም ምድር ለእርሱና ለዘሩ ትሰጥ ዘንድ ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረግህ አንተም ጻድቅ ነህና ቃልህን ፈጸምህ።›› ***ነህ 9፡7-8፡፡***
- **አዳምን ወይም ኖኅን ሳያነሱ አብርሃምን ያነሱት የአባቶቻቸው አባት አድርገው ስለሚቆጥሩት ነው፡፡**
- **እስራኤል አዳም ኃጢአትን ወደ ዓለም አስገብቶአል አብርሃም ግን እምነቱን በፍቅር የገለጠ አባት ነው በማለት ራሳቸውን ‹‹የአብርሃም ልጆች ነን›› በማለት ከአብርሃም ጋር ያያይዛሉ፡፡**
- ‹‹መልሰውም። አባታችንስ አብርሃም ነው አሉት። ኢየሱስም፦ የአብሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር።›› ***ዮሐ 8፡39፡፡*** **የተባለውም ይህንኑ የሚያስታውሰን ነው፡፡**
- **ከነዓናውያን፣ ኬጢያውያን፣ አሞራውያን፣ ፌርዛውያን፣ ኢያቡሳውያንም፣ ጌርጌሳውያንም ብርቱዎች የነበሩ ቢሆኑም ምድራቸው ግን በኢያሱ ወልደ ነዌ ዘመን በአይሁድ ተወስዶ ነበር፡፡**
- ‹‹በግብጽም ሳሉ የአባታችንን መከራ አየህ፥ በኤርትራ ባሕርም ሳሉ ጩኸታቸውን ሰማህ እንደ ታበዩባቸውም አውቀህ ነበርና በፈርዖንና በባሪያዎቹ ሁሉ በምድሩም ሕዝብ ሁሉ ላይ ምልክትና ተአምራት አሳየህ ዛሬም እንደ ሆነው ስምህን አስጠራህ። ከፊታቸውም ባሕሩን ከፈልህ፥ በባሕሩም መካከል በደረቅ አለፉ ጠላቶቻቸውን ግን ድንጋይ ለጥልቅ ውኃ እንዲጣል በቀላይ ውስጥ ጣልሃቸው። የሚሄዱበትንም መንገድ ታበራላቸው ዘንድ በቀን በደመና ዓምድ፥ በሌሊትም በእሳት ዓምድ መራሃቸው። ወደ ሲናም ተራራ ወረድህ፥ ከሰማይም ተናገርሃቸው ቅኑን ፍርድና እውነቱን ሕግ መልካሙንም ሥርዓትና ትእዛዝ ሰጠሃቸው የተቀደሰውንም ሰንበትህን አስታወቅሃቸው፥ ትእዛዝንና ሥርዓትን ሕግንም በባሪያህ በሙሴ እጅ አዘዝሃቸው። ለራባቸውም ከሰማይ እንጀራ ሰጠሃቸው፥ ለጥማታቸውም ከዓለቱ ውኃ አመጣህላቸው ወደ ማልህላቸውም ምድር ገብተው ይወርሱ ዘንድ አዘዝሃቸው።›› ***ነህ 9፡9-15፡፡***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

- ‹‹የተቀደሰው ሰንበትህን አስታወቅሃቸው›› በማለት የሰንበትን ቀን ትእዛዝ አስረዳን፤ ዛሬ ባህል ሆኖ የምናየው ሰፊ የሆነው የሰንበት መንፈሳዊ ሕይወት፣ ሥራና አገልግሎት የመነጨውም ከዚሁ ነው፡፡
- በዚህም የወደዳቸው እግዚአብሔርን፣ ሊያድናቸው ሰው ሆኖ የመጣውን መድኃኒታቸውን፣ ፋሲካውን (ስቅለቱንና ትንሣኤውን)፣ የኤርትራን ባሕር መከፈል (ጥምቀቱን)፣ የፈርዖንና የሠራዊቱን ስጥመት (ዲያቢሎስን ድል መንሳቱን) አስታወሳቸው፡፡
- እግዚአብሔር እስራኤልን ቀን በደመና ዓምድ ሌሊት በእሳት ዓምድ (በምስጢረ ሜሮንና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት) ይመራቸው ነበር፣ ቃል በቃልም ተናግሮአቸዋል (በመጽሐፍ ቅዱስ በምናገኘው የእግዚአብሔር ድምጽ በሆነው ቃሉ)፣ ረሐባቸውን ለማስረሳት መና አውርዶ (ሥጋውንና ደሙን ሰጥቶ) አጥግቦአቸዋል ፣ ለጥማቸው ዓለት አፍልቆ አርክቶአቸዋል (መንፈሳዊ እንካታን ሰጥቶአቸዋል)፣ የተስፋይቱን ምድር እንደሚወርሱ (መንግሥተ ሰማያትን) ተስፋ ሰጥቶአቸዋል፡፡
- ‹‹ነገር ግን እነርሱና አባቶቻችን ታበዩ፥ አንገታቸውንም አደንደኑ፥ ትእዛዝህንም አልሰሙም፥ ለመስማትም እንቢ አሉ፥ ያደረግህላቸውንም ተአምራት አላሰቡም አንገታቸውንም አደንደኑ፥ በዓመፃቸውም ወደ ባርነታቸው ይመለሱ ዘንድ አለቃ አደረጉ አንተ ግን ይቅር ባይ፥ ቸርና መሐሪ አምላክ፥ ለቍጣም የምትዘገይ፥ ምሕረትንም የምታበዛ ነህ፥ አልተውሃቸውም። ቀልጦ የተሠራውንም እምቦሳ አድርገው። ከግብጽ ያወጣህ አምላክህ ይህ ነው ባሉ ጊዜ፥ እጅግም ባስቈጡህ ጊዜ፥ አንተ በምሕረትህ ብዛት በምድረ በዳ አልተውሃቸውም በመንገድም ይመራቸው ዘንድ የደመና ዓምድ በቀን፥ የሚሄዱበትንም መንገድ ያበራላቸው ዘንድ የእሳት ዓምድ በሌሊት ከእነርሱ አልራቀም። ያስተምራቸውም ዘንድ መልካሙን መንፈስህን ሰጠሃቸው፥ መናህንም ከአፋቸው አልከለከልህም፥ ለጥማታቸውም ውኃ ሰጠሃቸው። አርባ ዓመትም በምድረ በዳ መገብሃቸው፥ ምንም አላጡም ልብሳቸውም…

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

- …አላረጀም፥ እግራቸውም አላበጠም። መንግሥታትንና አሕዛብን ከፍለህ ሰጠሃቸው የሐሴቦንን ንጉሥ የሴዎንን ምድር፥ የባሳንንም ንጉሥ የዐግን ምድር ወረሱ። ልጆቻቸውንም እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛህ ይገቡና ይወርሱ ዘንድ ለአባቶቻቸው ወደ ተናገርህላቸውም ምድር አገባሃቸው። ልጆቹም ገብተው ምድሩን ወረሱ፥ የምድሩን ሰዎች ከነዓናውያንን በፊታቸው አዋረድህ የሚወድዱትንም ነገር ያደረጉባቸው ዘንድ እነርሱንና ነገሥታቶቻቸውን የምድሩንም አሕዛብ በእጃቸው አሳልፈህ ሰጠሃቸው። ምሽጎቹንም ከተሞች የሰባውንም ምድር ወሰዱ መልካሙን ነገር የሞሉትን ቤቶች፥ የተማሱትንም ጉድጓዶች፥ ወይኖቹንና ወይራዎቹን ብዙዎቹንም የፍሬ ዛፎች ወረሱ በሉም፥ ጠገቡም፥ ወፈሩም፥ በታላቅ በጎነትህም ደስ አላቸው። ነገር ግን እንቢተኞች ነበሩ፥ ዐመፁብህም፥ ሕግህንም ወደ ኋላቸው ጣሉት ወደ አንተም ይመለሱ ዘንድ የመሰከሩባቸውን ነቢያትህን ገደሉ፥ እጅግም አስቈጡህ። ስለዚህ ለጠላቶቻቸው እጅ አሳልፈህ ሰጠሃቸው፥ አስጨነቁአቸውም በመከራቸውም ጊዜ ወደ አንተ ጮኹ፥ ከሰማይም ሰማሃቸው እንደ ምሕረትህም ብዛት ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳኑአቸውን ታዳጊዎችን ሰጠሃቸው። ባረፉም ጊዜ ተመልሰው በፊትህ ክፉ አደረጉ በጠላቶቻቸው እጅ ተውሃቸው፥ ገዙአቸውም ተመልሰውም ወደ አንተ በጮኹ ጊዜ ከሰማይ ሰማሃቸው፥ እንደ ምሕረትህም ብዛት ታደግሃቸው ወደ ሕግህም ትመልሳቸው ዘንድ አስመሰከርህባቸው ነገር ግን ታበዩ፥ ትእዛዝህንም አልሰሙም፥ ሰውም ባደረገው ጊዜ በሕይወት የሚኖርበትን ፍርድህን ተላለፉ ትከሻቸውንም ሰጡ፥ አንገታቸውን አደነደኑ፥ አልሰሙምም። ነገር ግን ብዙ ዓመታት ታገሥሃቸው፥ በነቢያትህም እጅ በመንፈስህ መሰከርህባቸው አላደመጡም፥ ስለዚህም በምድር አሕዛብ እጅ አሳልፈህ ሰጠሃቸው። ነገር ግን አንተ ቸርና መሐሪ አምላክ ነህና በምሕረትህ ብዛት ፈጽመህ አላጠፋሃቸውም፥ አልተውሃቸውምም።›› ***ነህ 9:16-31፡***
- **‹‹እነርሱና አባቶቻችን ትከሻቸውን ሰጡ፣ አንገታቸውን አደነደኑ፣ ትእዛዝህንም አልሰሙም›› ያለው የተፈጸመው ሙሴ በተራራው እንደሞተ አስበው ከወርቅ ጥጃ ሠርተው እንዳመለኩ አሮንንም ወደ ግብጽ መልሶ ይመራቸው ዘንድ በጠየቁ ጊዜ ነው፡፡**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

- ‹‹አንተ ግን መዓትህ የራቀ፣ ለቁጣ የዘገየህ፣ መሐሪ፣ ይቅር ባይ፣ ምሕረትህ የበዛ አምላክ ነህና አላጠፋሃቸውም አልተውሃቸውምም።›› በማለት የተጻፈልንም እግዚአብሔር በብሉይ ‹‹ኃይለኛና የሚቈጣ ነበር›› ብለው ለሚናገሩት የተሰጠ ምላሽ ነው። ታዲያ ባይ፣ ይቅር ረምሕረትህ የበዛ እየተባለ ‹‹ቁጡ›› ነበር እንዴት ሊባል ይችላል?
- እርሱ እግዚአብሔር (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) ትናንትናም ዛሬም ለዘላምም ያው ነው። በብሉይም በአዲስም ያለ፣ የነበረ የሚኖር እግዚአብሔር እርሱ ነው። ምሕረቱም ለዘላለም ነው።
- ከበደላቸው፣ ከአመጻቸው፣ ካለመታዘዛቸው፣ ጥጃ ሰርተው እግዚአብሔርን ከማስቆጣታቸው፣ ሕጉን ካለመፈጸማቸው፣ ነቢያትንም ከመግደላቸው በላይ ምሕረቱና ይቅርታው ታላቅ ናትና ቀን የደመና ሌሊት የእሳት ዓምድ አቁሞ መራቸው።
- በሙሴ በኩል መንገዱን ያሳያቸው ዘንድ መንፈሱን ላከላቸው። በበረሐ ሲጓዙ ልብሳቸው አላለቀም፣ መና መገባቸው፣ ከዓለት ውሃ አፍልቆ አጠጣቸው። የሚወርሷትን ምድር ሰጥቶ ጌዴዎንን፣ ዮፍታሔንና ሶምሶንን የመሳሰሉ መልካምነትን ገንዘብ ያደረጉ መሳፍንትን ሾመላቸው።
- እነርሱ ግን ትከሻቸውን ሰጡ፣ አንገታቸውን አደነደኑ፣ ትእዛዝህንም አልሰሙም። ይህም እግዚአብሔርን ላለመስማት ያሳዩት ትዕቢትና ትምክህት ነው። ምን ያህል ጊዜ እግዚአብሔርን ባለመስማታቸው ለጠላቶቻቸው ተላልፈው ተሰጥተዋል? አሁንም በምርኮው ጊዜ የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምሕረት ጠየቁ።

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱</u>

- ‹‹አሁንም አምላካችን ሆይ፥ ቃል ኪዳንንና ምሕረትን የምትጠብቅ ታላቅና ኃያል የተፈራኸውም አምላክ ሆይ፥ ከአሦር ነገሥታት ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በእኛና በነገሥታቶቻችን በአለቆቻችንም በካህናቶቻችንም በነቢያቶቻችንም በአባቶቻችንም በሕዝብህ ሁሉ ላይ የደረሰው መከራ ሁሉ በፊትህ ጥቂት መስሎ አይታይህ። በደረሰብንም ነገር ሁሉ አንተ ጻድቅ ነህ፥ አንተ እውነት አድርገሃልና፥ እኛም ኃጢአት አድርገናል፡፡ ነገሥታቶቻችንም አለቆቻችንም ካህናቶቻችንም አባቶቻችንም ሕግህን አልጠበቁም፥ የመሰከርህባቸውንም ትእዛዝህንና ምስክርህን አልሰሙህም። በመንግሥታቸውም በሰጠሃቸውም ታላቅ በጎነትህ፥ በፊታቸውም በሰጠኸው በሰባው ምድር አላመለኩህም፥ ከክፉም ሥራቸው አልተመለሱም።›› ***<u>ነህ 9፡32-35፡</u>***
- **‹‹እግዚአብሔር ሆይ ይህ አስቸጋሪ ጊዜ ሳትረሳ ስለ ኃጢአታችን የተሰጠን ቅጣት አድርገህ በመቁጠር መልካሙን ጊዜ መልሰህ ስጠን፡፡›› ብለው ለመኑ፡፡ ነህምያህ እንዲሁ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ አንተ ሁሌም ትክክል ነህ፤ በእኛ ያደረግህብንም የሚገባንን ነው፤ ነገር ግን ምሕረትህ ትደረግልን ይቅርም በለን፡፡›› አለ፡፡**
- ‹‹ እነሆ፥ ዛሬ ባሪያዎች ነን ፍሬዋንና በረከትዋን ይበሉ ዘንድ ለአባቶቻችን በሰጠሃት ምድር፥ እነሆ፥ በእርስዋ ባሪያዎች ነን፥ ስለ ኃጢአታችንም ለሾምህብን ነገሥታት በረከትዋን ታበዛለች ሰውነታችንንም ይገዛሉ፥ በእንስሶቻችንም የሚወድዱትን ያደርጋሉ፥ እኛም በጽኑ መከራ ላይ ነን።›› ***<u>ነህ 9፡36-37፡፡</u>***
- **‹‹እግዚአብሔር ሆይ ካንተ ጋር ስንሆን በምድራችን ነጻነት ያለን፣ ከጥገኝነት የተላቀቀን ነገሥታት ነበርን አሁን ግን በምድራችን ባሮች ሆነናል፡፡ ይህ ታላቅ መከራ ይበቃናል - አሁን ተመልሰን ቅጥሩንና ቤቶቻችንን እንሰራለን ትእዛዝህንም እንሰማለን›› በማለት የእግዚአብሔርን ልብ ለማራራት ጸለዩ፡፡**
- ‹‹ ስለዚህም ሁሉ የታመነውን ቃል ኪዳን አድርገን እንጽፋለን አለቆቻችንም ሌዋውያኖቻችንም ካህናቶቻችንም ያትሙበታል።›› ***<u>ነህ 9፡38፡፡</u>***
- **በመጨረሻም ሕዝቡ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ቃል ኪዳን ለመግባት ተስማሙ፤ ይኸውም ቃል ኪዳን በንስሐ የታደሰውና እግዚአብሔር ከሙሴና ከኢያሱ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ነበር፡፡**
- ***<u>ነህ 9፡17፣ 9፡27፣ 9፡20፣ 9፡31፣</u>*** ‹‹በደረሰብንም ነገር ሁሉ አንተ ጻድቅ ነህ፥ አንተ እውነት አድርገሃልና፥ እኛም ኃጢአት አድርገናል።›› ***<u>9፡33ን</u>*** **በቃል አጥንታችሁ ያዙ፡፡**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

- ምዕራፍ ዘጠኝ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳናቸውን እንዳደሱ ብሎም ወደ ቀደመው ድላቸውና ጠንካራ መንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደተመለሱ ይነግረንና ይህም ቃል ኪዳን በካህናቱ፣ በሌዋውያኑና በሕዝብ መሪዎች መታተሙን ያረጋግጥልናል፡፡ እነዚህም እነማን እንደነበሩ በነህምያ ጀምሮ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1 እስከ 27 ይተነትንልናል፡፡
- በቤተ ክርስቲያናችን ስንክሳር በየዘመናቱ የነበሩትን ቃል ኪዳናቸውን ያደሱትንና ብሎም ወደ ቀደመው ድላቸውና ጠንካራ መንፈሳዊ ሕይወታቸው የተመለሱትን ዲያቢሎስንም በጾና እምነትና በቀና ምግባር ያሸነፉትን ቅዱሳን ነገር ስንሰማና ስናነብ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ እንደሆነ መጽሐፈ ነህምያ ምዕራፍ 10 ከ1 እስከ 27 ያስታውሰናል፡፡
- ‹‹የቀሩትም ሕዝብ፥ ካህናቱም፥ ሌዋውያኑም፥ በረኞቹም፥ መዘምራንም፥ ናታኒምም፥ ከምድርም አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር ሕግ ራሳቸውን የለዩ ሁሉ፥ ሚስቶቻቸውም፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውም፥ የሚያውቁትና የሚያስተውሉትም ሁሉ ወደ ወንድሞቻቸው ወደ ታላላቆቻቸው ተጠጉ በእግዚአብሔርም ባሪያ በሙሴ እጅ በተሰጠው በእግዚአብሔር ሕግ ይሄዱ ዘንድ፥ የጌታችንንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ፍርዱንም ሥርዓቱንም ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ እርግማንና መሐላውን አደረጉ።›› ***ነህ 10:28-29፡፡***
- **ናታኒም፡-** ‹‹ሌዋውያንንም እንዲያገለግሉ ዳዊትና አለቆቹ ከሰጡአቸው ናታኒም ውስጥ ሁለት መቶ ሀያ ናታኒም አመጡ እነዚህም ሁሉ በስም በስማቸው ተጠሩ።›› ***ዕዝ 8:20፡፡*** እንደተጻፈልን ለአገልግሎት የተቀቡትን ቤተ መቅደሱን ለማገልገል የተሾሙትን የሚመለከት የዕብራውያን መጠሪያ ነው፡፡
- ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን የምንመጣ ከሆን ከዓለም ሰዎች መለየት አለብን፡፡
- እንደ ክርስቲያን በሥነ ምግባራችን፣ በአስተሳሰባችን፣ በመርሆዎቻችን፣ በአለባበሳችን፣ በአነጋገራችን፣ ተለይተን ብርሃን (ምሳሌ) ሆነን መኖር እንጂ የዚህ ዓለም ሰዎችን መስለን መመሳለስ የለብንም፡፡
- ከሙሴ ጀምሮ ማንኛውም ሰው ሴቶችን ጨምሮ ወንዶችም ሆኑ ልጃገረዶች ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አላቸው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

- ‹‹ሴቶች ልጆቻችንንም ለምድር አሕዛብ አንሰጥም፥ ሴቶች ልጆቻቸውንም ለልጆቻችን አንወስድም  የምድርን አሕዛብ ሸቀጥና ልዩ ልዩ እህል ሊገበዩ በሰንበት ቀን ቢያመጡ፥ በሰንበት ወይም በተቀደሰው ቀን ከእነርሱ አንገዛም የሰባተኛውንም ዓመት ፍሬና ዕዳን ማስከፈል እንተዋለን ብለው ማሉ።›› ***ነህ 10:30-31።***
- እግዚአብሔር ከማምኑት ወገን ለራሳቸው (ባል ወይም ሚስት) እንዳያደርጉ ደጋግሞ ያዘዛቸውን ጠብቀው ነበር፡፡
- ዛሬም ቢሆን ልጆቻችን ካላመኑት ጋር እንዳይጋቡ እንመክራቸዋለን፤ ሊያሳምኑ - ሊያስጠምቁአቸው ይገባልና፡፡
- በመንፈሳዊና ማኅበራዊ ግኑኝነታችንም መንፈሳዊና ማኅበራዊ ችግሮች እንዳይገጥሙን እንደጠፍ ከብት ከመነዳት ይልቅ በምክረ ካህን እንድንመራ ቤተ ክርስቲያን ታስታውሰናለች፡፡
- እስራኤል የምድሪቱ ሰዎች ከሆኑት - ከማያምኑት (አሕዛብ) በሰንበትና በበዓላት ባለመግዛትና ባለመሸጥ ሰንበትን ወደ ማክበር ተመለሱ፡፡
- ምድራቸውንም በሰባተኛው ዓመት ባለማረስ - እህል ባለመዝራትና ተክል ባለመትከል - ምድሪቱን በማሳረፍ - ዓመቱን ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ማክበር ተመለሱ፡፡
- ዕዳ ያለበትና መክፈል ያልተቻለው በሰባተኛው ዓመት ዕዳው ይሰረዝለት ነበር፤ ይህም በአዲስ ኪዳን የተገኘውን መንፈሳዊ በረከትና ይቅርታ የሚስረዳን ምሳሌ ነው፡፡
- ‹‹ ስለ አምላካችንም ቤት አገልግሎት፥ ስለ ገጸ ኅብስትም፥ ዘወትርም በሰንበትና በመባቻ ስለ ማቅረብ ስለ እህሉ ቍርባንና ስለሚቃጠል መሥዋዕት፥ ስለ በዓላትም፥ ስለ ተቀደሱትም ነገሮች፥ ለእስራኤልም ስለሚያስተሰርየው ስለ ኃጢአት መሥዋዕት፥ ስለ አምላካችንም ቤት ሥራ ሁሉ በየዓመቱ የሰቅል ሢሶ እናመጣ ዘንድ ትእዛዝ በራሳችን ላይ አደረግን። እኛም፥ ካህናቱና ሌዋውያኑ ሕዝቡም፥ እንደ አባቶቻችን ቤቶች በተወሰነ ጊዜ በየዓመቱ ወደ አምላካችን ቤት አምጥተን በሕጉ እንደ ተጻፈ በአምላካችን በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ ይቃጠል ዘንድ ስለ እንጨት ቍርባን ዕጣ ተጣጣልን›› ***ነህ 10:32-34።*** በቅድሚያ ራሱን ያልቀየረ ሰው ሌላውን ሰው ሊቀይረው ወይም ሊለውጠው አይችልም፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፱

- የእውነተኛ ንስሐ መታወቂያ ምልክቱ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በጥንቃቄ መፈጸምና መንፈሳዊ ምግባራትን በፍጹም የልብ ቅንዓትና በትጋት መፈጸም ነውና እስራኤልም በፍጹም ንስሐ ለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት አንድ ሦስተኛውን ለመስጠት ፈቀዱ፡፡ በኦሪት መጻሕፍት እንደተጻፈው አሥራ ሁለቱም ነገደ እስራኤል በየተራ በዓመት ለአንድ ወር ከሚነድ እንጨት ለሌዋውያኑ ቁርባን ማቅረብ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡
- ‹‹በየዓመቱም የመሬታችንን በኵራት የሁሉ ዓይነት ዛፍ የፍሬ ሁሉ በኵራት ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቤት እናመጣ ዘንድ፥ በሕጉም እንደ ተጻፈ የልጆቻችንና የእንስሶቻችንን በኵራት፥ የበሬዎቻችንንና የበጎቻችንን በኵራት በአምላካችን ቤት ወደሚያገለግሉት ካህናት ወደ አምላካችን ቤት እናመጣ ዘንድ፥ ›› ***ነህ 10፡35-36።***
- የዛፎችን ፍሬ በኩራት፣ የልጆቻቸውንና፣ የከብቶቻቸውን በኩራት ለምስጋና ወደ ሚያገለግሉት ካህናት ወደ እግዚአብሔር ቤት ያመጡ ነበር፡፡
- ‹‹ የእህላችንንም በኵራት፥ የእጅ ማንሣታችንን ቍርባን፥ የዛፍ ሁሉ ፍሬ፥ ወይኑንና ዘይቱንም ወደ ካህናቱ ወደ አምላካችን ቤት ጓዳዎች እናመጣ ዘንድ፥ ሌዋውያኑም ከከተሞቻችን እርሻ ሁሉ አሥራት ይቀበላሉና የመሬታችንን አሥራት ወደ ሌዋውያን እናመጣ ዘንድ ማልን።›› ***ነህ 10፡37፡፡***
- በመጽሐፈ ኢያሱ ሌዋውያን በተለያዩ አውራጃዎች ተበትነው የነገዶችን ሁሉ አሥራት ይሰበስቡ እንደነበር ተጽፎልናል፡፡ እነዚህም ሌዋውያን በመቅደሱ እግዚአብሔርን እያገለገሉ እነርሱም ከሚያገኙት አሥራታቸውን(የአሥራቱን አሥራት) ይሰጡ ነበር፤ ሁሉም በመስጠትና ስለ አሥራት የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅና በመፈጸም በሚገኘው በረከት  ደስ እየተሰኙ ይኖሩ ነበር፡፡
- ‹‹ሌዋውያኑም አሥራቱን በተቀበሉ ጊዜ የአሮን ልጅ ካህኑ ከሌዋውያን ጋር ይሁን ሌዋውያኑም የአሥራቱን አሥራት ወደ አምላካችን ቤት ወደ ጓዳዎች ወደ ዕቃ ቤት ያምጡት። የእስራኤል ልጆችና የሌዊ ልጆችም የእህሉንና የወይኑን የዘይቱንም የማንሣት ቍርባንን የመቅደሱ ዕቃዎችና የሚያገለግሉት ካህናት በረኞቹና መዘምራኑ ወዳሉባቸው ጓዳዎች ያግቡት እንዲሁም የአምላካችንን ቤት ከቶ አንተውም።›› ***ነህ 10፡38-39፡፡***
- ካህናቱም የነበራቸው ድርሻ ሌዋውያኑ የሰበሰቡትን የአሥራት አሥራት ወደ እግዚአብሔር ቤት ማቅረባቸውን መቆጣጠር ነበር፡፡ ***ነህ 10፡30 እና 10፡32*** በቃል አጥንታችሁ ያዙ፡፡

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org